ኢንተርፕርነርሽፕ ልማት ኢንስቲትዩት
Entrepreneurship Development Institute (EDI-Ethiopia)

ኢትዮስፐር የቢዝነስ ማስፋፊያ ዕቅድ ውድድር፡ የማመልከቻ መመሪያ

የኢትዮስፐር የቢዝነስ ማስፋፊያ ዕቅድ ውድድር በቀድሞው የኢንተርፕርነርሺፕ ልማት ማዕከል በአሁኑ የኢንተርፕርነርሺፕ ልማት ኢንስቲትዩት በ2012 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን ዕድገት ተኮር የሆኑ ቢዝነሶችን በመለየት የአንተርፕርነርሺፕ ክህሎታቸውን በማጎልበት ትርፋማ፣ ተወዳዳሪ እንዲሁም ዘላቂነት ያለው ቢዝነስ እንዲሰሩ የሚያግዝ ቀጥተኛ የሆነ ድጋፍ ለመስጠት ያለመ የቢዝነስ ማስፋፊያ ዕቅድ ውድድር ነው። የኢትዮስፐር ዓላማ ቢዝነሳቸውን ለማሳደግ የሚጥሩ ታታሪ ኢትዮጵያውያን አንተርፕርነሮችን መሸለምና መደገፍ ነው።

የማመልከቻ መመሪያዎች

ማመልከቻ ቅጹ አምስት ክፍሎችን ያቀፈ ነው።

1. የሽፋን ገጽ- ብቁ መሆንዎን የሚያረጋግጡ ጥያቄዎች እና ስለ ግላዊ መረጃዎት የበለጠ ለማወቅ የሚረዱ ጥያቄዎችን ይዟል።
2. የዋና አመልካቹ ፕሮፋይል- ስለ ትምህርትዎ፣ ልምድዎ እና ከኢዲአይ አገልግሎቶች ጋር ያለዎትን ትውውቅ ለመረዳት የሚያግዙ ጥያቄዎችን አካቷል።
3. የቢዝነስ ፕሮፋይል- ስለ ንግድዎ ጥቅል መረጃ ለማወቅ የሚያስችል ጥያቄ አቅፏል።
4. አሁናዊ የቢዝነስ አፈጻጸም- ስለ ቢዝነስዎ አሁናዊ መረጃ የሚሰጡ ጥያቄዎች አሉበት።
5. የቢዝነስ ማስፋፊያ ዕቅድዎ- ስለአጠቃላይ የቢዝነስ ማስፋፊያ ዕቅድዎ፣ ስለአስቀመጥዎቸው ግቦች፣ ስለሚተገብሯቸው ስልቶች(ስትራቴጂዎች) እና በዘርፉ ስላለዎት የተፎካካሪነት ብልጫ የሚያነሱ ጥያቄዎችን አካቷል።

ለውድድሩ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች

- አመልካቹ/ቿ ኢትዮጵያዊ/ት መሆን አለባቸው።
- አመልካቹ/ቿ ቢያንስ ለአንድ ዓመት በስራ ላይ የሚገኝ የንግድ ድርጅት ከፍተኛ ባለድርሻ መሆን ይኖርበታል።
- ቢዝነሱ በማንኛውም ዘርፍ የተሰማራ ሆኖ ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ሊኖረው ይገባል።
- ቢዝነሱ ከ **0-50** የሚሆኑ ሠራተኞች ሊኖሩት ያስፈልጋል።

የማመልከቻ መመሪያዎች

- ማመልከቻውን ከማስገባትዎ በፊት የማመልከቻ ቅጹ ሁሉም ክፍሎች በሙሉ መሞላት ይኖርባቸዋል።
- ለአብዛኛው አመልካቾች የማመልከቻ ቅጹን ለመሙላት በግምት 1 ሰዓት ይወስዳል። ማመልከቻውን እስከ የካቲት **21/2015** ዓ.ም ማስረከብ/ማስገባት ይገባል።

- ማመልከቻውን በእንግሊዝኛ፣ በአማርኛ እና በኦሮምኛ ቋንቋ ማስገባት ይቻላል።
- ሌሎች ሰነዶች ወይም አባሪዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም። ከውድድሩ ማመልከቻ ማስገቢያ የመጨረሻ ቀን በኋላ የሚመጡ ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።
- በማመልከቻው ላይ የሚካተቱ መረጃዎች ሚስጥራዊነት የተጠበቀ ነው። እሸናፊ የሚሆኑ የሁሉም ድርጅቶች በማመልከቻቸው ላይ የተገለጹ መረጃዎችን በሙሉ የማጣራትና የማረጋገጥ ስራ ይሰራል። በማጣራት ሂደቱም ማናቸውም መረጃዎች ሃሰተኛ ወይም የተሳሳቱ ሆነው ከተገኙ ከውድድሩ ውጪ የሚያደርጉና አመልካቹ ከማናቸውም የኢ.ዲ.አይ. አገልግሎቶችና እገዛዎች ተጠቃሚነት ውጪ ያደርጋል።

- ለማንኛውም ሊኖርዎት ለሚችሉ ጥያቄዎችዎ ይህንን ቀዳሚ የማመልከቻ መቀበያ ኢሜይል አድራሻ በመጠቀም ጥያቄዎትን ማቅረብ ይችላሉ apply.ethiospur@gmail.com እንዲሁም በሚከተለው አማራጭ የኢሜይል አድራሻ ኮፒ ያድርጉልን info@edi-ethiopia.org የኢሜይል መልዕክትዎ በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ያገኛል። በአማራጭነት የሚከተሉትን ስልክ ቁጥሮች መጠቀም ይችላሉ:: +251-115-571-150 ወይም በነፃ የስልክ መስመር 8658.

የማመልከቻ መንገዶች

- በኦንላይን ለማመልከት bit.ly/3TzEl1E
- ቁብሳይቱ ላይ የሚገኘውን ማመልከቻ ቅጽ በማውረድ ሞልተው በሚከተለው ኢሜይል አድራሻ መላክ ይችላሉ apply.ethioSpur@gmail.com እና info@edi-ethiopia.org
- የማመልከቻ ቅጹን አትመው በመሙላት፣ በአካል በማስገባት፣ ማመልከቻውን በፍላሽ ወይም በሲዲ በማድረግ ከሚከተሉት የኢ.ዲ.አይ ቢሮዎች አንዱ ጋር በመሄድ ማመልከቻዎትን ማስገባት ይችላሉ።

አዲስ አበባ (ዋና መስሪያ ቤት)
ነጋ ሲቲ ሞል (ዘመን ባንክ ፊት ለፊት) 3ተኛ ፎቅ, ካሳንቺስ አዲስ አበባ
ስልክ: +251-115-571-150
ኢ-ሜይል: apply.ethioSpur@gmail.com / info@edi-ethiopia.org

አማራ ክልል: ባህር ዳር
ከአማራ ፋይናንስ ቢሮ አጠገብ
ስልክ: +251-582-205-161 ወይም +251-583-209-709
ኢ-ሜይል: info.amhara@edi-ethiopia.org

ኢንተርፕርነርሽፕ ልማት ኢንስቲትዩት
Entrepreneurship Development Institute (EDI-Ethiopia)

ኦሮምያ ክልል፡ ቢሾፍቱ

ቢሾፍቱ መሬት አስተዳደር ህንጻ, 4ተኛ ፎቅ

ስልክ: +251-114-307-826 ወይም +251-114-300-993

ኢ-ሜይል፡i-info.oromia@edi-ethiopia.org

ደ/ብ/ብ/ህ እና ሲዳማ ክልሎች፡ ሃዋሳ

ኦሞ ባንክ

ስልክ፡ +251-462-125-359

ኢሜይል፡ info.snnpr@edi-ethiopia.org

የመጨረሻ የውድድሩ ማመልከቻ ቀን፡ የካቲት 21/2015 ዓ.ም

ማስታወሻ፡ ከኢንተርፕርነርሺፕ ልማት ኢንስቲትዩት ስትራቴጂካል ትኩረት ውስጥ አንዱ የሆነው ጥናትና ምርምሮች ላይ በመሳተፍና ምርምሮችን በማድረግ አገልግሎቶችን ማሻሻልና የስራ ፈጠራን (አንተርፕርነርሺፕን) ማሳደግ ነው። በመሆኑም የኢትዮ-ስፐር ውድድር ማመልከቻዎትን ሲያስገቡ ያስገቡትን መረጃዎችዎን ጥናትና ምርምር ለማድረግ ለሚፈልጉ አካላት ለማጋራትና ለተጨማሪ መረጃዎች እርስዎን ማግኘት እንደሚችሉና ምርምራቸውን እንዲሰሩ ፈቃድ እንደሰጡ ይቆጠራል።